# ★ ዴሞክራሲያ ★

★

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ዴሞክራሲያ ቅጽ 8፣ ቁጥር 1 የካቲት 23/1973 ዓ.ም

## ከየካቲት እስከ የካቲት

የመራራውን ትግል አንዱ ሰባቱ - ሰባት የካቲቶች - አሳለፈን፣ መጪውን ደግሞ እሁንም እንደ ወትሮው፣ አጥንታችንን ዝዝዝን፣ ደማችንን አርከፍክፈን፣ ከፍ ባለ የመስዋእትነት ስሜት ልንቀበለው በምንሰናዳበት ወቅት የየካቲትን ዑደት ማተር አጭርገን ማለፍ፣ በስተፊታችን ለሚጠብቀን ጉዞ ዓይነተኛ ምርኩዝ ይሆነናል::

ሆኖም የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ ሁኔታ መለስ ብለን ከመመልከታችን በፊት ከዚሁ ጋር የማይነጠለውን የኢምፔሪያሊዝምንና የሶሻል ኢምፔሪያሊዝምን ዓለም አቀፋዊ ክስተት በናስተውል፣ ኢምፔሪያሊዝምና ሶሻል ኢምፔሪያሊዝም በጅ አዙር ቅኝ ግዛት አደን ላይ በሚናቸነፈሩት ባሁኑ ጊዜ፣ በማንኛውም ክፍለ ዓለም የሚነሳ የፖለቲካ ጥያቄ ከዓለም አቀፍ የፖለቲካ ሁኔታ ተነጥሎ ሊታይ ከቶ እንደማይቻል እንገነዘባለን::

ዛሬ፣ የዓለም አቀፍ የፖለቲካ ሁኔታ ከወትሮው የተለየ ነው:: ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የተጋፊነቱን ሚና በፊታውራሪነት ይዞ ዓለምን በከንቱ ለመሥፈር፣ አያሌ ጊዜ ከርኮን ቢነዘርም፣

- የቻይና አብዮት ድል መቀዳጀት፣
- የኩሪያን ህዝባዊ አብዮት ለማጨናገፍ ሙከር መክሸፉ፣
- እንዲሁም በመጨረሻ በኢንዶ ቻይና ህዝቦች ትግል በመረታቱ፣

በዓለም አቀፍ የፖለቲካ መስክ ዝሎና ጣምና ይገኛል::

ይህ ቸገሬት በአሜሪካን ህብረተሰብ ውስጥ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ኅብረተሰባዊ ቀውሶችን በመፍጠሩ፣ በዓለምም ፖለቲካዊ ሁኔታ አሜሪካ የምትከተለው የውጭ ፖሊሲ ከፍተኛ ተቃውሞ ስላስነሳ፣ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም፣ አፈር ሸምቀቀ ብሎ፣ የፊታውራሪነቱን 'ማእርግ' /ሚና/ ለተቀናቃኙ ለሶሻል ኢምፔሪያሊዝም ለቀቅ ለጊዜው ሰገደድ እንዲል የግድ ሆኖበታል::

ከዚሁም ዘንድ ሶሻል ኢምፔሪያሊዝም ራሱን የዓለም ኅብረተሰብ ዳኛ፣ ፖሊስ፣ ቁጥ፣ 'አስታራቂ'፣ ሞግዚት፣ አድርጉ በመሰየም፣ በህዝቦች ብሔራዊ ክብርና ነፃነት በማሾፍ፣ ቀዳዳ ባገኘበት፣ ወሸለሸል ባየበት ሁሉ፣ ራሱ በቀጥታም ሆነ ወይንም ተቀጥላ በሆኑ ቅኤ መንግሥታት ወታደሮች አማካይነት ዘው ማለት ጀመረ:: እነሆም፣ አንጎላ፣ ሞዛምቢክ፣ ከዚያም ኢትዮጵያ፣ ካምፑቺያና አፍጋኒስታን ከመዳፉ ወደቁ::

የፊውዳሉ ቡርዧውን ሥርዓት መሠረት ንዶ፣ የተማገረበትንም የኢምፔሪያሊዝም ቅላጅ በጣጥሶ እያስገመገመ መገስገስ የጀመረውን የየካቲት ህዝባዊ አብዮት ለመገደብ፣ ሶሻል ኢምፔሪያሊዝም ያለ የሌለ መሣሪያ ለፋሽስታዊው መንግሥት በማራገፍ የእጅ አዙር ቅኝ ገዥነትን ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም መረከቡን በውል አረጋገጠ:: የካምፑቺያንም መንግሥት በቬትናም በማስወረር ሕጋዊ መንግሥቱን ገለብጦ የራሱን ሎሌ መንግሥት አቋቋመ:: አፍጋኒስታንም ላይ የራሱን ጦር አዝምቶ አገሪቱን በማጥለቅለቅ ለራሱ የሚበጀውን መንግሥት ተክቶ በዓለም ፊት በማን አለብኝነት አኩርፎ ቆመ::

ይህ ዕብሪት ግን ለትግሉ ክብሪቱ እየሆነ ቃጠሎ አሥነሳበት እንጂ ጭቁን ሕዝቦችን አፉ አላስነሳለትም፤ አንገት አላስደፋበትም፣ ይልቁንም ቢሮክራሲያዊ ፀብልጥ ተጋሪና ወራሪ እየሆነ በመጣበት ጨና መ[illegible] [illegible] እየከዳው፤ የሚወድቅበቱ ዕዘቀት እየጐደጐደ በመሔዱ ፤ በኢትዮጵያ የሚካሄደው ሕዝባዊ ጦርነት፤ በኤርትራ፤ በካምቹቺያና በአፍጋኒስታን የሚካሄደው የአርነት ትግል፤ እንዲሁም አሁን በቅርቡ የተቀጣጠለው የፖላንድ ሕዝብ ትግል ስፋትና ጥልቀት እያገኙ እንዲነጉዱ፤ ያልነቃበት እንዲነቃበት፤ የነቃበት እንዲሰለፍበት "እሹሁ ለአጣሪው" እንዲሆንበት አድርጓታል።

እነሆም ለፍትሕና ለሰላም ጭቁኖች የሚቀበሉት ፍዳ፤ የሚያካሄዱት መራራ ትግል ሲያከትም የሚችለው ሀልውናቸው ከጦርነት የሚሰርፀው ቢሮክራሲያዊ ኢምፔሪያሊዝምና የርሱም ሎሌ የሆኑ ፋሺስታውያን መንግሥታት ሲደመሰሱ ብቻ ስለሆነ በቢሮክራሲያዊ ኢምፔሪያሊዝምና በግብር አበሮቹ ላይ የሚሳበው ምላጭ እየበረከተ፤ የጦር ግንባሩ እየተለጠጠ በመሔዱ ላይ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች አብዮት ሰባት የካቲቶች እንደማሳለፉ መጠን፤ የጨቅላነት ዘመኑን አልፎ የወተት ጥርሱን ሸርፎ ገንቱ ያለውን ሲነጭበት፤ጠጠር ያለው ሲቆረጥምበት የሚያስችለውን የዘለቄታ ጥርሱን እንዳወጣ ብሊቱና ሁኗል፡፡

ባሁኑ ወቀት ፋሺስታዊው መንግሥት ብልተ – ስስ – አውታረ – ለሌ ሁኖ፤ በየካቲቱ ሕዝባዊ ቁጣ ሥልጣኑን አሁኑኑ ተተፋታለሁ ብሎ በማንቁርቱ እንደተያዘበትና እንደቱገደገደበት ጊዜ አይደለም፡፡ ከታክቲካዊ የትግል ወቀት አንፃር የካቲት በፈጠራቸው ሁኔታዎች ጊዜው የሚጠይቃቸውና የሚፈቅዳቸው ታክቲካዊ ጥያቄዎች መፈክሮችና የትግል ስልቶች የፖለቲካውን ሁኔታ በማጋጋምና አብዮቱ መራመድ እስከሚችለው ጋት ድረስ በመግፋት፤ ቱእንግዲህ ለዘለቄታው መከተል ያለበትን ስትራቴጂያዊ የትግል አቅጣጫ አሲይዘውት ከስሟል፡፡

የየካቲት አብዮት የፈጠረው አዲስ የፖለቲካ ሁኔታ ባሁኑ ጊዜ ተቁይሮ እንደመገኘቱ መጠን፤ የአብዮቱ ወገን ደከም ያለበትና የፋሺስታ መንግሥት ወታደራዊ ክንዱ ደንደን ብሎ የመጣበት ጊዜ ነው፡፡ ለዚህም መሟጤ ካደረጉት ምክንያቶች፤

- በአብዮቱ ኃይሎች ውስጥ የደረሰው ውስጣዊ ችግር
- በአብዮታዊያንና በዲሞክራሲያዉያን ኃይላት መሃል ያገሪቱ ቱጨባጭ ሁኔታና የትግላችን ልዩ ጠባዮች የግድ የሚሉት ይዘትና ቅርጽ የኅብረት ግንባር ለመመሥረት አለመቻሉ፤
- ፋሺስታዊው መንግሥት ከቢሮክራሲያዊ ኢምፔሪያሊዝም በገፍ እርዳታ ማግኘት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ዛሬ፤ የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ በየካቲቱ አብዮት "ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም!" የሚል ክቡር ዓላማን የሚገልጽ መፈክር ባንቀረቀረበት አንደበቱ ይህንን የሚያረክስ " የኢሰፓአኮ ተልዕኮ ይሳካል" የሚል የጥፋት ተልዕኮን የሚያረዳ፤ ፋሺስታዊ አምባገነንነትን የሚያረጋግጥ መፈክር ሲያ እየተናነቀው እንዲያላዝን ቱደርጓል፡፡

ፋሺስታዊው መንግሥት በፈከረ፤ በደነፋ ቁጥር፤ የጭቁኖችን አገር ሙቀ ለማጥበቅ ዓዩ ባሰማ ቁጥር "አንደኛ ሲያር ጥርስ ይገፋቀፋታል" ሁኖበት፤ የዐመጽ ረመጥ ቁሽቱን እያሳረረው፤ ገንባሩ ላይ ለተነጣጠረው ጠመንጃ ዙሪያውን ገረገራ ለሆነበት ታንክና መትረየስ ዕፁብ ድንቅ እያለ ማጨብጨብ፤ እሰይ በግ እያለ ጥርሱን ማሳየት ነፍሱን ለማሳደር በሚከፍለው ውድ ዋጋ ላይ አነስተኛ ምርቃት ሁናለች፡፡

ሰፊው ሕዝብ ከልሂቅ እስከ ደቂቅ እንደ አንድ ልብ መካሪ፤ እንደ አንድ ቃል ቱናጋሪ ሁኖ በአንድነት አፈፍ ብሎ የተነካባቸውና አንገቱን ለስለት ደረቱን ለጥይት፤ ሥጋውን ለአራዊት ያደረገባቸው የአብዮቱ መሠረታውያን ትንታጌ ጥያቄዎች የት ደረሱ ብሎ ለሚጠይቅ፤ መልሱ እንደገና ሊፈነዱ ተቀብረዋል፤ነው፡፡ ለየካቲት አብዮት ምክንያት የሆኑት ቀራኒዎች የትንፀባረቁባቸው ጥያቄዎች ማለትም የፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄ፤ የሰብዓዊና የዲሞክራሲያዊ

መብት ጥያቄዎች፣ ኢኮኖሚያዊና ኅብረተሰባዊ ጥያቄዎች፣ የመሬት ጥያቄ፣ የብሔር ጥያቄ፣ የኤርትራ ጥያቄ፣ .....ወዘተ መልካቸው ተቀየረ እንጂ አሁንም አለተፈቱም፣በቁዩ መሰለ ፀሎም ገምኝ ተገንዘው "ተቀበረ" እንጂ መፍትሔ አገኝተው ሕይወት አለዘሩም ፋሺዝምና ዲሞክራሲ ሆድና ጀርባ እንደመሆናቸው መጠን፣ የፋሺስት መንግሥት ጠቅላላ ስትራቴጂ በሰፊው ህዝብና በነኚህ መሠረታውያን ጥያቄዎች መሃከል ገድግዳ ሆኖ መቆም ጠባቂ የሚጠይቀው ጣጣ ነው:: ስለዚህም ነው፣ በፋሺስት መንግሥት ላይ ተቃውሞ ለማሰማት መከጀል፣ የሥራ ማቆም አድማ ለማድረግ መሞከር ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ማሰብ፣ ባንድ ቃልም ፣ ነፃ የሆኑ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን ማለም ሞትን የሚጠሩ "ነውረኛ"ምኞቶች የሆኑት::

አንድ ኅብረተሰባዊ አብዮት የሚነሳው፣ በምርት ግንኙነትና በምርት ኃይሎች መሃል ያለው ቅራኔ፣ እንዲሁም በሰፊው ጭቁን ሕዝብና የፖለቲካ ሥልጣኑን በያዘው የገዥ መደብ መሃል ያለው ቅራኔ ጡዘ፣ ሰፊው ጭቁን ሕዝብ እንደወትሮው እየተንገዘገዘ ኑሮውን ሊገፋ ከማይችልበት አፋፍ ላይ በመድረስ፣ የቀረው አማራጭ ዐመጽ ብቻ ሆኖ የሚያገኝበት ቅጽበት እንደመሆኑ ሁሉ፣ በየካቲት 66ም የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ተነሳስተው ለዲሞክራሲያዊ መብትና ለሕዝባዊ መንግሥት ሲታገሉ፣ የነርሱ ፍላጐት ብቻም ሳይሆን፣ የኢትዮጵያም ኅብረተሰባዊ መዋቅር ያለቀለት ያፈጀለት ሆኖ ኅብረተሰቡን እንዲትም ሥንዝር ይዞ ሊጓዝ ባለመቻሉ ከፍተኛ ዲሞክራሲያዊ ውሳጤ ወይንም ሽግግር እንዲያደርግ ታሪክ በዚያቸን እፍታ ሰንጐ የጠየቀውም ስለሆነ ነበር::

እነሆም በነገሥታትና በገዥ መደቦች ፍጹም ሥልጣንና ለእለና ፈንታ የዲሞክራሲ ለእለና እንዲተካና፣ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የማቋቋም፣ የሰራተኛ የአርሶ አደርና የሌሎች ኅብረተሰብ ክፍሎች ማኅበራት የማቋቋም መብት ማለትም ነፃ የሆነ የፖለቲካዊና ኅብረተሰባዊ እንቅስቃሴ የማድረግ መብት እንዲኖር የየካቲት አብዮት ያቀረባቸው መጠይቆች ናቸው::

እነህ ጥያቄዎች በመብት ክለል ብቻ የሚታዩ ሳይሆኑ፣ ጠቅላላው የኅብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ኅብረተሰባዊ ሥርዐት የሚጠይቀው ታሪካዊ ሂደት ነው::

የኅብረተሰቡ እድገት ይህንን ታሪክ የቀየሰውን የአብዮት ጉዳና ይዞ እንዳይጓዝ መንገዱን ዘግቶ ኢዲሞክራሲያዊ በሆነ ስርዓት መስደድ ማለት ለየካቲቱ አብዮት መፈንዳት ምክንያት የሆኑት ቅራኔዎች በየአቅራፉ ፈንጂ ሁነው፣ ጠምደው እንዲጠብቁት ከማድረግ በተቀር እንኳን እንዲፈቱ እንዲረገቡም አያደርግ::

በዚሁ ሥርጥ በመጓዝ የመንግሥቱና የግብር አበሮቹ መንግሥት ሥዩመ ቦሻለ ኢምፔሪያሊዝም ሁና ቀብዓ ፋሺዝምን ተቀብቶ በትረ ከዊቢን ይዞ የማይጠየቅ ሥልጣኑን ለማረጋገጥ በቦሻሊዝም ስም "ኢሰፓአኮ" የሚባል ፓርቲ በማቋቋም፣ ነፃ በሆኑ ሕዝባውያን ድርጅቶች ፈንታ ለፋሺስታዊ አገዛዝ በሚያመች ቅርጽና ይዞት የተደራጁ ማኅበራትን በሰፊው ሕዝብ ላይ አጠመደ:: ሰፊው ሕዝብ በነፃ ሊመክርበት ሊዘክርበት የሚችልበት መፈናፈኛ መድረክ ካገኘ ከፈላጭ ቆራጩ መንግሥት ጋር ያቆራኘው የከረረ የቅራኔ ገመድ በአብዮታዊ ሥለት እንደሚቆርጠው ፋሺስታውያን ምግባሮቹ ያስጠነቅቁታልና፣ ምንም ዓይነት መልክና ይዘት ይኑራቸው —ብቻ— ነፃ የሚል ቅጽል የተቀዳጁ ኅብረተሰባዊ ማኅበራት ይሉ እንቅስቃሴዎች ቀደት በቀደት ስለሚያደርጉት፣ ነፃ የስፖርት ማህበራት እንኳን ሳይቀሩ እስከማፍረስ ደረሰ::

ከመቶ ሺህ በላይ በሆነ ወታደርና ፖሊስ መታጠሩ ሳያንሰው፣ (ሕዝቡን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር፣ የአስትንፋሱን ሙቀት አቀጣጪያ ሳይቀር ለመለካት ጀቸለ ዘንድ የዓለምን ሕዝብ በማስለቀስና የሩሲያን ሕዝብ ይህ ነው በማይባል ስቀቀንና ሽብር ጭብጥ ኩርትም አድርጐ በመያዝ ከፍተኛ "የሥራ ውጤት"ባገኘው ኬጂቢ ስቱላው የመሰከበ የስለላ ድርጅት እንዲሁም በኩባና በምሥራቅ ጀርመን የስለላ ድርጅቶች አቀነባባሪነት፣ ሰፊ የስለላ አውታር በየቀበሌ ማኅበሩ ሳይቀር ዘርግቶ የያንዳንዱን ነዋሪ እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለመቆጣጠር

አያቀደው ነገር አይፈጽመው ግፍ የለም::

ሠራውን ህዝብ በገዛ ራሱ መደብ ተገለ ፓዝቢ ባይተዋር ያደረገ፤ ዩሰራው ህዝብ ነበረ ጠባዩ እንቅስቃሴ የሚያስበረገገው፤ ሥልጣን ላይ የመቆየት ዋስትናው ከሰላሳው መረጡና ከወታደራዊ ድርጅቱ የሰረፀ ሕዝቡን እንደጭራቅ የሚፈራ መንግሥት "አብዮታዊና ሶሺያሊስት" ነኝ ይለናል::

በአፈታሪክም ሆነ በተጨፈ ታሪክ በኢትዮጵያ ውስጥ በአለቆቹና በፍጆቱ መጠን፤ በገፍና በጭካኔው ደረጃ ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቅ፤ ለትውልድ ትውልድ ሲዘገገን የሚኖር ሲፋቅ፤ ሊታጠብ፤ ሊደበዝዝ የማይችል አረመኔያዊ ተግባራት የፈጸመ የደይን መንግሥት "ሶሺሊስት" ነኝ ሲለን፤ እኛ ለንረዳው የምንችለው፤ "ራሴን በራሴ ካላን የሊጸሊጠስሁት" በሚል የቧለት ዘይቤ ብቻ ነው::

ይህ የፋሺስቶችና የሶሺል ኢምፔሪያሊስቶች የገፍና የሽብር አገዛዝ መላ ሀገሪቱን ወህኒ ቤት ባደረገበት ባሁኑ ወቅት ከዚህ መሪር አገዛዝ፤ እያሸሹ መሞትን፤ እንደ ክብር መት በመቁጠር፤ ዳዩ ጥሰው፤ በረሃ ሰንጥቀው ቁር እሩሩን ችለው፤ ያቴጥርን ለገሰና ተማጥነው፤ አደማስን ጥካ አድርገው ተኰረቤት ሀገር በደመ ነፍሳቸው የደረሱ / ከኤርትራና ከኢትዮጵያ ክፍለ ተ ሀገራት የተሰደዱ ስደተኞች/ ቁጥር በዓለም ላይ ካሉት ስደተኞች በበዛቱ የአንደኛነት ደረጃ መያዙ ከቶ ሊያስደንቀን አይገባም:: አሁንም ወደ ሱማልያና ወደ ኬንያ ስደተኞች እየጐረፉ ናቸው፤ ከሀመራ እርሻ ጣቢያዎች ዘመን ባለፈስተ የባርነት እስራር እንደመንጋ እየተነዱ ገለበታቸውን የሚከሰክሱ፤ ከእንስሳት ያነሰ 'እንክብካቤ' የሚደረግላቸው 'በሆጋዊ' መንገድ ከየቀበሌ ማኅበሩ ተፈንገለው የመጡ አርሶ አደሮችና ሥራ አጦች፤ በዓመፅ ከየጣቢያው ሰብረው እየወጡ፤ ኳሊ እየጣሉ ወደ ሱዳን ከመግባት አላቋረጡም:

እነህ ሁሉ በፋሺስታዊው መንግሥት ዓይን "አብዮቱ የመጣባቸው፤ ጥቅማቸው የተነካ መሳፍንትና ርዝራዞቻቸው ናቸውና! "ፋሺስቱ መንግሥት በየጐረቤት አገሩ ለውካን እየላከ "ኢትዮጵያውያን ስደተኞች አገራችሁ ተመለሱቻሁ 'በሶሺሊዝም ግንባታ' ተካፈሉ" እያለ ቢማጠንም፤ "ማን ያርዳ? የቁረ" ነጋሪ በዚህ ሁሉ ያይን ምስክር ፊት ሊያታለል የሚችል የቻለውን ቢኖር አምነት ያዋነን ብቻ ነው::

የሶሺል ኢምፔሪያሊዝምና የጐቾሎቹ አገዛዝ ምን ያህል መሪር፤ ምን ያህል አስከፊና አስቃቂ እንደሆነ በይበልጥ ለመረዳት ከኢትዮጵያም ፈቀቅ ብለን ብናዳምጥ ከቬትናም፤ ከቤፑቢ፤ ከካምፑቼያና ከአፍጋኒስታን፤ በየጊዜው እንደኛ አገር ስደተኛ ሁሉ "ከገዛ ሀገር የሞት ሞት፤ የባዕድ አገር እንጊት ሞት "እያሉ የሚጐርፉት ስደተኞች የሚታርኩት "ጉን ይሰማ ደር"በሚል የሚደመደም ነው::

በኢኮኖሚውስ በኩል?

አሁን የሚታየው ትርምስምስና ቀውስ ከየት ፈለቀ ብንል ከፋሺስት የአገዛዝ ዘይቤና ፖሊሲ የመነጨ መሆኑን እንመለከታለን:: ፋሺስቶች ምንም ዓይነት ነፃ የሆነ ኅብረተሰባዊ እንቅስቃሴ እንዳይኖር እንደመፈለጋቸው መጠን ጠቅላላውን የኢኮኖሚ ችግር ከፖለቲካው ገንጥለው 'መፍትሔ' ለመስጠት ይሞክራሉ:: በዚህም ቁመር መሠረት፤ ያለ ገጠር አብዮት ሊፈታ የማይችለውን የመሬት ጥያቄ ፤ ፋሺስታዊው መንግሥት፤ በባር ከበር ቱው መደብና በአርሶ አደሩ መሃል ካለው ፖለቲካዊ ግንኙነት በመገንጠል፤ በኢኮኖሚያዊ መልስ፤ 'መፍትሔ' ለመስጠት ከንቱ ሙከራ አድርጓል::

የመሬቱ አዋጅ በመሶረቱ በጨሰኛና በባለመሬት መሃል የነበረውን የፊውዳል ግንኙነት ጥሶታል:: እስከዚህ ድረስ ማለፊያ ነበር:: ይሁን እንጂ በኢኮኖሚ ላይ የተመሰረተ የመደቦች ግንኙነት፤ አብዮታዊ በሆነ የፖለቲካ ለውጥ አብዮታዊ በሆነ መንግሥት መቋቋም መድንዋስትና ካላገኘ በስተቀር "ውሃ ቀዳ፤ ውሃ መልስ"ይሆንና የኢኮኖሚ ግንኙነታቸው በመቋረጡ ቦታቸውንና ጥቅማቸውን ያጡ የነበሩ በዝባዥ መደቦች ተመለሰው ኅብረተሰባዊ መሰረት፤ እንዲያም ሲል የፖለቲካ መሶረት በመገንባት ቀስ በቀስ የኢኮኖሚ ጥቅማቸውን እንደሚያስመልሱ ከታሪክ—በተለይም ከሩሲያው አብዮት ታሪክ—እንማራለን::

ጓዋ. ቅጽ ፪፣ ቁ. 1

የመሬት ለዋጭ ከፖለቲካ አንፃር፣ መሬት ከባለ መሬቶ እጅ ወደ አርሶ አደሩ እጅ ሲዛወር መቻሉን፣ ማስመለከቱ አንድ ትልቅ የፖለቲካዊ ቁም ነገር ነው:: ሆኖም ባዋጁ፣ ጢሰኛና ባለርስቶች ባለባቸው አካባቢ ጢሰኛው፣ ያርሰው የነበረውን መሬት ይዞ እንዲቆይ አደረገ እንጂ መበረት ሩብ ጋሻ / 10 ሄክተር/ ለያንዳንዱ ጢሰኛ አልተደለደለም:: በመሰረቱ ከሁሉም አስቀድሞ መሬትን እኩል የማከፋፈል እርምጃ ለመውሰድ በአርሶ አደሩና በመንግሥት መካከል አብዮታዊ የሆነ የፖለቲካ ግንኙነት ስለሚጠይቅ አብዮታዊ መንግሥትን የግድ ይፈልጋል::

አብዮታዊ መንግሥቱ በሕዝብ ላይ ምንም ዓይነት ተጽእኖ ሳያደርግ፣ ራሱ አርሶ አደር በመንግሥቱ ላይ በሚያሳድረው የእምነት ደረጃ መጠን፣ በሠረተ ለሠረተ የማሻሻውንና በግል ባረስ የምርጠውን፣ እንደየቢጤቱ በተለይም ሃገሪቱ ያለችበት ታሪካዊ ደረጃ ተመዝኖ የቁጠባዊ አቅሟ በሚፈቅደው መጠን በማስተናበር ወደፊት አርሶ አደር በገዛ እምነቱ በኅብረት የሚያርሰበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ በገበያ ላይ የሚፈጠሩትን የምስቅልቅል ሁኔታዎች በማስተካከል የዋጋ ቁጥጥር ማድረግ አርሶ አደሩ ምርቱን ለገበያ የሚያቀርብበትን መንገድ ማመቻቸት ለአርሶ አደሩም የሚያስፈልጉት እሉቁ እቃዎች በየጊዜው ከገበያ የማይጠፉበትን መንገድ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል::

ፋሺስታዊ መንግሥት ግን አርሶ አደሩን ስለማያምነውና በነፃ እንዲደራጅ ስለማይፈቅድለት፣ አርሶ አደሩም ፋሺስታዊው መንግሥት ለኔ የቆመ ነው የሚል እምነት ስለሌለው፣ የመሬት እኩል ማከፋፈል እርምጃ ፖለቲካዊ እንደመሆኑ መጠን ፋሺስታዊው መንግሥት ሊያካሂድ የቻለው የቻለውም፣ የመሬት ድልድል ብቻ ነው፣ ይህም ቢሆን በርከት ባሉ የሰሜን አካባቢዎች ሊናጋጋ አልቻለም::

ይኸውም የመሬት ድልድል ምን ክስተት አያሳየ ነው ብለን ስንጠይቅ፣ የመሬት ድልድሉ፣ ጢሰኞች የሚያርሱትን መሬት ይዘው እንዲቆዩ ካላደረገ አንዳንዶቹ ሰፊ መሬት ያያዙ፣ በርካታ ምርት ሲያመርቱ፣ ጠባብ መሬት ያለው ባነሰ ምርት ይወሰናል/ በደበረ መሬትና በበር መሬት መሃል ያለው ልዩነትም እንዲሁ/ ይህም በገበያም ላይ አለመጣጠንን በማስከተል፣ በርካታ ምርት ያላቸው፣ ሀብት ወደ ማከበትና የግል እርሻ ወደ ማስፋፋት እየተገፋፉ ናቸው::

ይህም ሁኔታ እየቀጠለ በመሔዱ፣ በአርሶ አደሩ መሃል የሀብታምና የመለስተኛ ገበሬ ክፍሎች መፈጠር ጀምረዋል:: ይህ ሁኔታ እንዳለ ሆኖ፣ የገበሬ ማህበራቱ፣ አርሶ አደሩ በፈቀደው መልክ እንዲያገለግሉት የፈጠራቸው ሳይሆኑ፣ መንግሥት በሚበይደው መንገድ በዓዋጅ ቢጋጠው መሰረት የተቋቋሙ ስለሆኑ፣ የመንግሥት ትእዛዝ ማስፈጸሚያ ክርኖች እንጂ የሕዝብ ተጠሪያቹ፣ እንጂ ጠባቂያች አይደሉም::

እንግዲህ የመሬት አዋጁ በጠቃላይ ሲለኩ ስንመለከተው የፊውዳል ግንኙነትን ቢሰብርም የተጓደሉትን አያሌ ነገሮች ለማሟላት የፋሺስታዊው መንግሥት ኢ-ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ከቶ አይፈቅድለትም::

ይህ ቀጥ አምባገነ የጠፋው ፋሺስታዊ መንግሥት አገሪቱ ለታደግ የምትችለው "ሁሉም ሸንጡን ገትሮ ሌት ተቀን ሲሰራና ምርቱ ከፍ ሲያደርግ ነው" በሚል ሲጣ መፈክር ተነሳስቶ አገሪቱ ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት ካፒታል እንዳሚያስፈልጋት እንጂ፣ ባሏት አቅምና በደረሰችበት ታሪካዊ ደረጃ ከየትኛው የኢኮኖሚ ክፍል እንደምታገኘው በውል ሳይለይ "አረንጓዴ ዘመቻ" ብሎ አወጀ፣ ሰፊው ጭቁን ሕዝብ በየተሰማራበት የሥራ መስክ፣ የቁም ስቆሉን ካየ ካሳሩን ከጠበሰ በኋላ፣ በፕሮፖጋንዳና የሥራ ቀራልን ከፍ በማድረግ ብቻ ምርት ማብዛት እንደማይቻል፣ የተመኘት ካፒታልም በፋሺስቶች ሸብአረብ እንደማይገኝ ተግባር ስላረጋገጠ፣ እንደኢትዮጵያ ባሉ ኋላ ቀር አገሮች ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት የሚያስችል በቂ ካፒታል ሊገኝ የሚችለው ከርሻ ምርት በሚገኘው የውጭ ንግድ መሆኑን ተገነዘበ::

ተገንዝቦም አልቀረ፣ ከአረንጓዴው ባሉን በራፍ ለታለፍ ያልቻለቸውን አስ ቲሳቡን /"አረንጓዴ ዘመቻ"/ ሁኔታ ባያበዛ ለስለስ አድርጐ በመሳብ፣ ባንድ በኩል የሶሻል–ኢምፔሪያሊዝምን የመሣሪያ እዳ የሚገፈግፍበት፣ በሌላ ወገን ደግሞ የኢንዱስትሪ ተቋም "የሚያስፋፋበት" የርሻ ምርት ፖሊሲ ማውጣት ፈለገ:: ለዚህም የነበረው ምርጫ፣ ማእከላዊነት ያለው አንድ ወጥ የሆነና መንግሥት ራሱ በቀጥታ እጁን የሚነክርበት ከቻለም የሚቆጣጠረው፣ በመንግሥትና በገበሬዎች ትብብር የሚካሔድ የርሻ ፖሊሲ መትለም ነበር:: መንግሥት የምርት እድገትን በቀጥታ ተቆጣጥሮ የተወሰነ ወይም ከፍተኛ ምርት በየጊዜው እንዲኖር ዋስትና ካላገኘ ከርሻ ምርት ላይ ተመሥርቶ በውጭ ንግድ የሚገኝ ካፒታል ይኖረኛል ብሎ መጓፈር አይችልም:: ይህ ደግሞ በተለይም የሶሻል–ኢምፔሪያሊዝምን እዳ–በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሔደው ሕዝባዊ ጦርነት፣ የኤርትራ ሕዝብ ትግል፣ የልዩ ልዩ ጭቁን ብሔሮች ትግል እስከ ቀጠለ ድረስ፣ በቋሚነት የሚቀጥል እዳ–መክፈል አለተቻለም ማለት ይሆናል::

ስለዚህም የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ያለበት ማእከላዊና አንድ ወጥ የርሻ ፖሊሲ ለመከተል የግል እርሻዎችን መከለከልና በቦታቸው የገበሬዎች የኅብረት እርሻ መተካት የግድ ሆነበት:: ከዚህም ግዴታ ተነስቶ ከምሥራቅ አውሮፖ አገሮች ተመክሮ በመንደርደርና እነዚህ አገሮች መደመርያ ከነበራቸው አብዮታዊ የፖለቲካ ሥልጣን ተመክሮና ታሪካዊ ደረጃ ጋር የኢትዮጵያን ሁኔታ አመሳስሎ በማየት፣–ቃልና ቃል እንዳመሳሰሉ..–የኅብረት እርሻ መቋቋም አለበት አለ፣ የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማህበራት አወጀ::

ፋሽስቱ መንግሥት ገና፣

–የመሬቱን አዋጅ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ሳያውል፣

–ከአርሶ አደሩ ጋር ያለው የጋመ ቅራኔ ሳይፈታ፣

በአርሶ አደሩ በጐ ፈቃድ ላይ ሙሉ በሙሉ የማመሠረተውንና ለኅብረት እርሻው መደላደል በሚሆን ኤኮኖሚያዊ መሰረት ላይ የሚያቀረውን የአምራቾች ማኅበር ደርሶ ማወጁ ፋሽስቶች ብቻ ሊፈቱት የሚችሉት ራስይ ነው::

ወደ ዐውኑ እንመለስና፣ የኅብረት እርሻና የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማቋቋም ጉዳይ ከሁሉ አስቀድሞ ከርሻ ምርት የሚገኘው ትርፍ መንግሥታዊ ጥቅምና እዳን ለመክፈል ሳይሆን፣ ለሰርቶ አደሩ ሕዝብ ጥቅም የሚውል መሆኑን የሚያረጋግጥ አብዮታዊ የሆነ የፖለቲካ ሥልጣን፣ ማለትም የላባደሩ ፓርቲ ሥልጣን መጨበጥን የግድ ይላል እንዲህ ዓይነቱ መንግሥትም ከአርሶ አደሩ ጋር አብዮታዊ ውህደት ስለሚፈጥር የኤኮኖሚ ፖሊሲውን በማስረዳትና በማሳመን የላባደሩንና የአርሶ አደሩን አጋርነት በማጠናከር፣ ሰፊው ጭቁን ሕዝብ የገዛ ራሱ መንግሥት ብሎ እንደ ዐይን ብሌኑ አድርጐ እንዲጠብቀው ያደርጋል::

ሁለተኛ፣ የኅብረት እርሻ ከተቋቋመ በኋላ ይህ እርሻ የሚደላደልበት ቴክኒካዊ መሰረት ያስፈልገዋል:: በከተሞች በላባደሩ የሚሰሩት አላቂ እቃዎች ለአርሶ አደሩ በበቂ መድረስ አለመድረሳቸውን መከታተል፣ የዋጋ ቁጥጥር ማድረግን፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን የሥራ ክፍፍል በማጥናት፣ አስፈላጊ ለሆኑ ጉድ–ኢንዱስትሪዎች ትኩረት መስጠትና ማዳበርን፣ የትምህርትና የሕዝብ ጤና ጥበቃ አገልግሎት መሟላትን ሁሉ ያጠቃልላል

ሦስተኛ፣ በመሬቱ አዋጅ መሰረት መሬት በሚገባ ተከፋፍሎ፣ አርሶ አደሩ፣በዚያች ተሸንሽና በተሰጠቸው ቁራጭ መሬት ላይ በግሉ መቧገት ከድኅነት እንደማያላቀቀው ከገዛ ራሱ ተመክሮ እንዲማርና እንዲረዳ ማድረግ ያስፈልጋል::

ይህን ከመሳሰለ ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ሁኔታ ባሻገር የኅብረት እርሻና የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማቋቋም ዓዋጅ እንደ ተሰማ የመሬት ድልድል በተካሔደባቸው የደቡብና ምዕራብ ኢትዮጵያ ክፍለ ገዛቶች ውስጥ ከፍተኛ የአርሶ አደሮች አመጽ የተነሳው ለዘመናት በጢሰኛነት ሲማቅን የኖረው አርሶ አደር፣ በያዘው መሬት እርጋ በተባለ

በአራተኛ አመቱ "መሬት የጋራ ናትና፣ በኅብረት አረስ" የሚል አነጋ ለመጣበት፣ መሬቱን እን
ደገና ሊነጠቅ ነው የሚል ፍራቻ ስላደረበት፣ የምታየኝ ዐመፃ ናት ያለ ሲያምፅ ከሲዳሞና
ከባሌ ወደ ሶማልያና ኬንያ ከኰረፈው ሥፍር ቁጥር የሌለው ሕዝብ ከፊሉ በዚህ ምክንያት
የተሰደደ ነው::

ለማጠቃለለም በየጊዜው እየተባባሰ የሚሄደውን የኢኮኖሚ ቀውስ ለመረዳት እንችል
ዘንድ፣ የዚህ ፋሺስት መንግሥት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጠባይ ምንድነው ብለን ስንጠይቅ፣ መንግ
ሥታዊ ካፒታሊዝም ነው የሚል መልስ እናገኛለን:: መንግሥታዊ ካፒታሊዝም የሊባደሩ መደብ
ሶሻሊስታዊ ኢኮኖሚ ከመገንባቱ በፊት መሸጋገሪያ የኢኮኖሚ ፖሊሲው እንደመሆኑ መጠን "ፍየ
ል ወደዚህ ቅዝምዝም ወደዚያ" እንዲሉ፣ የሊባደሩ አገዛዝ መንግሥታዊ ካፒታሊዝም ወደ ሶሻ
ሊዝም ሲያመራ፣ የቢሮው ከበርቴ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ መንግሥታዊ ካፒታሊዝም ደግሞ እንደ
ምሥራቅ አውሮፖ አገሮች የጨቋኞችና የበዝባዦች ጥቅም ማስጠበቂያ የሆነውን የከበርቴውን
መንግሥት ካፒታሊዝም የሚያጠናክር ሆኖ እናገኘዋለን::

የፋሺስቱ መንግሥት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ንድፈ ሐሳባዊ መሰረት ስንመለከት፣ የቀኝ ክ
ንፉ ንዑስ ከበርቴና ፋሺስቶች ኢኮኖሚን ከፖለቲካ ነጥለው "ድህነትን እናጠፋለን" ከሚል
ቅዠታቸው የሰረፀ ነው:: ከዚህም የተነሳ ፋሺስታዊው መንግሥት ከሰፊው ህዝብ በተለይም
ከሰርቶ አደሩ ጋር ያለውን ቅራኔ ለማድበስበስ፣ መሰረታዊ ፖለቲካዊ የሆኑ፣ በኢኮኖሚያ
ዊ መልክ የሚገለጹ ችግሮችን በኢኮኖሚያዊ መንገድ ብቻ "መፍትሔ" ለመስጠት ይሞክራል::
እንደዚህም ስነጣጥቃቸው ሲያበቃ ግን በፕሮፖጋንዳው "ሁሉም ነገር 'ለሶሻሊዝም' ገንቢ"
ብሎ ያሸፋል::

ፋሺስታዊው መንግሥት፣ አረንጓዴ ዘመቻ ሲያውጅ፣ "በናት አገር ጥሪ" ስም ትርፍ ሰ
ዓት ሲያሰራ፣ ሕዝብ እያግበሰበሰ ሆራ ሲያራግፍ፣ የሰፈራ ፕሮግራም ሲያውጅ፣ ያደረገው
ን ሲያደርግ፣ ትርፉ የሰፊው ሕዝብ ለብ ውለቅ እንጂ፣ በየጊዜው ይብሱን እየተወሳሰበ ከ
ሚሄደው ኢኮኖሚ ፖሊሲ ፈቀቅ ሊያደርገው ከቶ አይቻለም::—እንኳንስ ድኅነትን ሊያጠፋለት
ኢንዱስትሪ ሊያስፋፋለት::

ድህነትስ ሊጠፋ የሚችለው፣ የበዝባዥ ሥርዐት ተደምስሶ፣ ሕዝባዊ መንግሥት ተቋቁ
ሞ ሰርቶ አደሩ ራሱ በምርቱ ውጤቱና ፖሊሲ ላይ እየተካፈለ ሲሰራ እንጂ ሰርቶ አደሩ የ
ሩቅ ተመልካች ሆኖ ከፖለቲካ ገለል ብሎ በመንግሥት አድራጊ ሰሪነት፣ ፈላጭ ቆራጭነት በ
ሚካሄድ ሥርዓት እየማስነ አይደለም::

የኤርትራ ጥያቄ እንዲሁም የብሔር ጥያቄ፣ የኢትዮጵያ አብዮት መፍታት ካለበት
ዋና ዋና የፖለቲካ ጥያቄዎች ውስጥ ናቸው:: የብሔር እንቅስቃሴዎች፣ በተለይም የኤርትራ
ጭቁን ሕዝብ ለነፃነቱ የሚያደርገው ትግል በቀደመ አብዮት ኢትዮጵያ ለዓመታት ተካሄደው
ከነበሩ፣ የአፄ ኃይለሥላሴን ፈላጭ ቆራጭ የንግሥና አገዛዝ ለማዳከም፣ ብሎም ለየካቲቱ አብዮት
መፈንዳት ምክንያት ከሆኑት ሥርዐታዊ መንሥኤዎች አንደኛው ነበር:: የብሔር እንቅስቃሴዎ
ች ጥያቄ የኢትዮጵያ አብዮት፣ ከፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄ ቀጥሎ፣ ባንገብጋቢ ደረጃ መፍታት
ያለበት ጥያቄ ነው::

ፋሺስቱ መንግሥት በብሔር ጥያቄ ላይ ያለው አቋም ግልጽ ነው፣ ገና ሥልጣን በያ
ዘ በስድስተኛው ወር፣ በኤርትራ ውስጥ ከዚያ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ጦርነት በመ
ክፈቱ ቅራኔውን በቢሮክራሲያዊ መንገድ ከመፍታት ይልቅ በጠመንጃ ኃይል ለመፍታት ያነሳው
ፋሺስታዊ ልክፍት እንደተጠናወተው ግልጽ ሆኖ ነበር:: አሁንም የብሔር እንቅስቃሴዎቹ ባለፉ
ት ሁሉ ጦርነት ማባባስ እንጂ በቢሮክራሲያዊ መንገድ ለመጨረስ ምንም ዐይነት ፍንጭ አላ
ሳየም:: ፋሺስቶች የብሔር ጥያቄን በጠመንጃ ለመፍታት ያደረጉት ሙከራ የኤርትራን ሕዝብ
ትግል ለማዳፈን የተደረገው ጥረት፣ እንቅስቃሴዎችን ከማጠናከርና አዲሶችን ከመፍጠር ሌላ
የፈየደው ነገር አላየንም::

ተዋ. ቀጽ 8፣ ቁ. 1

የብሔርና የኤርትራ ጥያቄ የፋሺስቱ መንግሥት አገዛዝ እስካለ ድረስ መፍትሔ የማያገኝ በመሆኑ፣ ለዚሁ ጥያቄ መፈታት ዋነኛው ዋስትናው፣ አብዮታዊ አቸናፊ የፖለቲካ ሥልጣን ጭቁን ሕዝቦች እጅ መግባት ነው:: የኢህአፓ አቋም በዚሁ ጥያቄ ላይ ርቱዕና ግልፅ ነው:

ብሔሮችና ብሔረሰቦች ማንም ሊገስባቸው የማይገባ ሉዓላዊ ክብርና እኩልነት ስላላቸው፣ የራሳቸውን እድል በሚሹት መንገድ ለመቀየስ፣ ለመወሰን፣ ማንም ሊሰጥ ሊነሳቸው የማይችል ሙሉ መብት አላቸው፤ ይህ መብት ተረጋግጦ፣ የብሔር ንቅናቄዎች በተነሱባቸው አካባቢዎች ጥያቄዎችን እንደ ተጨባጩ ሁኔታ በተናጠል በማየት አስፈላጊውን መፍትሔ መስጠት ያስፈልጋል:—

ይላል ኢህአፓ:: በኤርትራም ጥያቄ ላይ ኢህአፓ አቋሙ የማያወላውል ነው፤

— የኤርትራ ሕዝቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው ለመወሰን፣ ተገንጥለውም ነፃ መንግሥት እስከ ማቋቋም ድረስ ያላቸውን ሙሉ መብት ያውቃል፣

— የኤርትራ ጭቁን ሕዝብ ለነፃነቱ የሚያደርገውን ትግል ይደግፋል፣:

— የኤርትራን ነፃ መሆን ይደግፋል::

ፋሺስቱ መንግሥት ሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ የብሔር እንቅስቃሴዎች እየተወለዱ፣ ያሉትም እየጠናከሩ ይሔዳሉ:: ከኤርትራ ሕዝብ ትግል ሌላ፣ የኦሮሞ፣ የኦጋዴንና አፋር ሕዝቦች የሚያደርጉትም እንቅስቃሴ እንደ ቀጠለ ነው:: "እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው"በሚል መንፈስ የፋሽስቱ መንግሥት ያዐጣው የዘጠኝ ነጥብ የኤርትራ ፖሊሲ፣ ሪጅናል ኦቶኖሚ ....ወዘተ ሥንዝር ሊራመድ አልቻለም፣ የኤርትራና የብሔር ጥያቄዎች መፍትሔ ሊያገኙ የሚችሉት ማእከላዊው የፋሺስት አገዛዝ አብዮታዊና ሕዝባዊ በሆነ መንግሥት ሲተካ ብቻ ነውና::

የጭቁን ሕዝቦች መሠረታዊያን ጥያቄዎች ሊመለስ የሚችለው፣ በላባደሩ የሚመራው ሕዝባዊ መንግሥት ሀልውና ሲኖረው እንደመሆኑ ሁሉ ይህንን እውን ለማድረግ በሚደረገው ገድል የላባደሩ ሚና ግንባር ቦታውን ይይዛል::

የኢትዮጵያ ላባደር ትግል አኩሪ ታሪክ ያለው፣ ሰፊ ተመክሮ የገበየ ነው:: ከየካቲት አብዮት በፊት ከአሥር ዓመታት በላይ ኢሠአማ በተካለው የሰራተኛ ድርጅት አማካይነት፣ ሥርዓቱና ሁኔታው በሚፈቅደውና፣ ከዚያም ውጭ አቅሙ ሊያስኬደው በቻለው መጠን ሁሉ መራራ ትግል አካሂዷል:: በተናጠል ይደረጉ ከነበሩ እንቅስቃሴዎች ሌላ፣ በጠቅላላ የሥራ ማቆም አድማ ደረጃ ከየካቲቱ አብዮት በፊት ሁለት ጊዜ ቀጠሮ ሳይሳካለት ቢቀርና አንጋፋ መሪዎቹንም መሥዋዕት አድርጎ ቢያቀርብም፣ እነዚህ መራራ ተመክሮዎች ለየካቲቱ እንቅስቃሴ መሰረት ጥለውለታል::

የየካቲቱ አብዮት እንደፈነዳ፣ የላባደሩ መደብ ሚና ቦግ ብሎ መታየት ጀመረ፤ እንደመደብም በአንድነት ተሰለፈ፣ አደመ፣ ታገለ፣ ደማ፣ ተሰዋ፣: በየካቲት ለመጀመሪያ ጊዜ የተካካ የሥራ ማቆም አድማ በማድረግ ለሌሎቹ ኅብረተሰብ ክፍሎችም በማስተማር የሥራ ማቆም አድማና ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ የየካቲት አብዮት ዓይነተኛ መለኮ እንዲሆን አደረገ:: የላባደሩ መደባዊ ትግል ፋሺስቱ መንግሥት ሥልጣን ላይ በተቆናጠጠበት ጊዜም በመፋፋም ቀጥሏል:: በለየ ለዩ ጊዜ ከፋሺስቶቹ ጋር ካደረገው ከፍተኛ ትንንቅና ትግል ሌላ በ1968 ዓ.ም ሜይ ዴይ በኢሕአፓ አማካይነት ተደራጅቶ በመላ ኢትዮጵያ ያዘጋጀው ፀረ ፋሺስት ሰልፍ ባገኛቸው ታላላቅ የፖለቲካ ድሎች ላይ ረብቦ የሚታይ ነው::

ኢሕአፓ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ዐቅሙ በፈቀደለት መጠን በላባደሩ መሃል ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል:: ኢሠአማ በባርነት አዉጅ ከተዘጋ በኋላ፣ ለላባደሩ እንቅስቃሴ አስፈላጊውን አመራር ለመስጠት ይቻል ዘንድ፣ ኢሕአፓ ከላባደሩ መሃል የነቃው ክፍል በኢሌአማ ሥር እንዲደራጅና የላባደሩ ትግል አስተማማኝ በሆነ መንገድ እንዲቀጥል ጥርጊያውን ከፍቷል::

የየካቲቱ አብዮት፣ ኢሕአፓ ገና ዉርጃ ሳለ የመጣ እንደመሆኑ መጠን ዋና ትኩረቱን ያደረገው ላባደሩ ባነሷቸው ጥያቄዎች ላይ ተገሎን ግጨፎና ፋሺስቶችና ከላሽ ባንዳዎች ተጽዕኖ ሥር እንዳይጋለጡ ማድረግ ላይ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ላባደር መደብ እንቅስቃሴ ከላባደሩ ፓርቲ ጋር የተያያዘ የረጅም ጊዜ የፖለቲካ ልምድ ያለ ነበረው በመሆኑ ፓርቲው ቀጥተኛ አመራር በመስጠትና በመያዝ ደረጃ ገና ለጋ ቢሆንም፣ ከአብዮቱ በኋላ በነበሩት ሦስት ዓመታት ያገኘው የፖለቲካ ትግል ልምድ ላባደሩ የፓርቲ አባላት እንደ ገንቢር ቀደምትነታቸው ትግል ከፍተኛ ጊና እንዲጫወቱ ያደረገ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ላባደር መደብ በቁጥሩ አነስተኛ ቢሆንም፣ አሁንም የአብዮቱ መሪ፣ አሁንም የአገሪቱ ታሪክ ቀያሪ ወሳኝ ኃይል ነው፡፡ የላባደሩ ቁጥር ማነስ፣ የላባደሩ መሰስተኛና ከፍተኛ ፕሮግራም የሚያነገን ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና ሶሻሊዝምን የመመስረት ታሪካዊ ተልእኮውን ግንም የጊር ከበርቴ ወገን ሽር፣ ሶሻል—ኢምፔሪያሊስቶች እንደሚያነበንቡት "ካፒታሊስታዊ ያልሆነ" ጉዳናቸውን ሊያጣናው፣ ወይንም የመሪነት መንበሩን ሊቀማው አይችልም፡፡

ባጠቃላይ ሲታይ አሁንም በኢትዮጵያ ውስጥ ፋሺስቱ መንግሥትና ሶሻል ኢምፔሪያሊዝም በጠምራነት ባገሪ ረድፍ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሌላው ረድፍ የተፋጠጡበት አሰላለፍ የዐቢይ ቅራኔነትን ቦታ እንዳያዘ ይገኛል፡፡ ይህ የቅራኔዎች ምስስ በሕዝባዊ ወርነቱ የአሳት ላንቃ ከፍገግጉ፣ በመጋባያ ትግሉ ጋይ ከለ ተገረሰሰ በስተቀር ገላዉ ላይ የተዋቀፈጉት ሌሎች ዘይን ተረፍ ቅራኔዎች ሊደረመሱ አይችሉም፡፡

ፋሺስታዊው መንግሥት የሶሻሊስት ሥርዓት ደመስርታል ብሎ መጠገቁ "ለም አለኝ በሰማይ "እንደሚገባለው መሆኑን የያንዳንቱ የኪሳት ወደት አንቀ ኪንደኛው ቧና ሰጥቶ አያስረገጠ ያለፈው ነው፡፡ የፋሺስታዊው ሥልጣኑን ለማጠናከሪያ ጥቅሞችን ለማግኘት የተያዙ እንደመሆናቸው መጠን በተግባር የእይ ቢፈተኑ "ሕዝባዊ" ዐዘናቸው የጠነዘለ ፋሺስትነታቸው በየጊዜው ቀንደ እየቦ ከመሔድ ሊያመልጥ አልቻለም፡፡

የየካቲቱ አብዮት ላስገኛቸው ለአካቹ የምኅበራዊ ሥርዓት ታሪክ ከመደቡለት የትቢያ ዐተቀት ለመጣል አርአዷ እንቀጥቀጥ ግርማ ለገበ፣ ኃይሉ ኃያላት ሆኖ፣ ወደር በሌለው አብዮታዊ ጉራት የተነሳን ሰፊ ሕዝብ፣ በሶሻል ኢምፔሪያሊዝም መጢኛ ብሔራዊ ክብሩ ተደምጦ፣ በከፍቢ ዐታደሮች ገልምጧ፣ አርጩ ሰብአዊ ኩራቱ ባኑቶ፣ በፋሺስታዊ መዋቅሮችና የስለላ መረቦች፣ አጅ ላገሩ ተኩሎኩደ፣ ትንደበቱ ቻቦቶ፣ ኢሎሂ ትያለ ሕማማት ውስጥ ቢገኝም፣ የድቀትን መራራነት እንደሚያውቀ ሁሉ፣ የትንሣኤን ጣፋጭነት ይገመዋል፤ ያማትቁር የማታ ቢሳ ለመሆኑም ጥርጥር የለውም፡፡

ነገረ ተካቢዊ አብዮትን ያሀል ምድር የሚያናውፅ መንኰራኩር ግንባክ ቀላል ነገር አይደለም፤ ከጫዳ ቀለ ፍላት፣ ከቀለ ቀለት አጣት ይቀኮራቸታለና የአብዮቱ ኃይላትም በዚሁ አኳያ መሃል መዓከም ዓየለ መበር ታቶ ይፈራረቁባቸዋል፡፡ የኛም አብዮት በዚሁ ጉዳና በመጓዝ አዝጋሚ ምዕራፍ ላይ ይገኛል፣ ሆኖም ይህ ጊዜያዊ መዓከም ቁስ በቁስ እያለ ለሚያድግ የዘለቄታ ጥንካሬ መንደርደሪያ ሲሆን የፋሺስታዊው መንግሥት ጊዜያዊ ጥንካሬ ግን ውሉ አድሮ ለዘለቄታ ድካምና ብሎም መደምሰስ የሚተካ ነው፡፡

ኢሕአፓ ሕዝባዊ ወርነቱን በመምራት ዕድሜና ሙከሮ ከሚፈቅዱለት በላይ ትንግርታዊ ገድሎች ተቀብሏል፣ በውጭም በውስጥ ጠላቶችም ቁስሏል ደምቷል፤ ግን ጥቀኑ ሕዝብ የጫለበትን አደራ ከግቡ ሳያደርስ፣ ደሙ አይነጥፍም፡፡ በቁር በገደል የወደቁው የአብዮታውያን ደገኖች ዐጽም የጉራጥ እያየው፣ የጥቁኖች የደታ ጎሊናው ውስጥ መሽ እያወረደበት፣ የሐፍረት ከለጫዳ ለብሶ፣ ዐይኑን ሰብሮ ከትግሉ ጫዳ ሸከከ ብሎ አይወጣም፣ ይህ ከፍተኛ ታሪካዊ ነጋር፣ ትግሉ እየጠለለ ሲመጣ እያዘቀጠ የሚቁር አስር የሆኑ ደካሞች በታኞችና አበሮቻቸው እንደሉ ቁርታ ነው፡፡ የኢሕአፓ ጽዮ ፈንታ፣ የተከበረውን ጠገኖ የተከጠሰውን ያጥር፣ የጋከመውን አበረታቶ፣ ኃይሉን አሰባስቦ፣ ትንፋሹን መልሶ፣ ደገኖች አባላቱ ይህ

ጓኳህ በማይቢል ሉዓላዊ መሥዋእትነት የከፈልነትን እዲስ የተገለ ምዕራፍ ማደስ ማስፋት እንጂ ማጥበብ ማጠፍ አይደለም::

ስለሆነም የጠላት ጥቃት ተቋቁሞ፣ ብቱናን መከቶ፤ አሁንም እንደወትሮው በትግሉ እየወደቀ ሊነሳ፣ እየመታም ድል ሊያደርግ ተጥቀን አጥብቀ የተመከር መዝገብቀን ሸከፍ በከፍተኛ አብዮታዊ መንፈስ ፋሺስታዊ መንግሥት ላይ ብረቀን ወድሯል::

አብዮት ቁስ በቁስ እያደገ እየተነደገ እንደሚሔድ፣ "ትንቢ ምሏጥ አገር ተሏጥ"እንዲሉ፣ አንዲት ትንቃግ ሰደድ እሳት እንደምታከነሳ፣ በዚህች የጭቆናች ምንቸት ማሰሮ በሆነች አገራችንም፣ እየነፈረ እየተንተከተከ ያለ ጭቀን ሕዝብ፣ ወገሏሏቀን ገለበጠ እንደሚገነፍል ታሪክ ያሜ ምስክራችን ነውና ከፋሺስቶችና ከሺራ—ኢምፔሪያሊስቶች ጋር የምናደርገውን እስጥ አገባ በከፍተኛ አብዮታዊ ወኔና ድፍረት "የምሥራች ለወዳጆቻችን፣ መርዶ ለጠላቶቻችን!"እያልን ቀጥለናል::

የምሥራች ለወዳጆቻችን! መርዶ ለጠላቶቻችን!

ትግሉ ይቀጥላል!

እ ና ቸ ን ፋ ለ ን !!